## እግዚአብሔርን ማክበር (ክፍል 1)

### ለመክበር የከበረውን ማክበር፣ ዘጸ 4፡10፣ ዘፀ19፡9-10 -11-22 )

### እግዚአበሔርን ማክበር በምን ይገለፃል

ወደ እግዚአብሔር በምንቀርብበት ጊዜ (ቃሉን ለመማር/ለማጥናት/ለመስማት፤ ለማምለክ፤ ለመጸለይ) ሊሆን ይችላል እግዚአብሔርን ማክበር በምን ይጀመር አለ፡-

**1/ የኃጢአት እድፈትን በማሰወገድ/ንስሃ ገብቶ ከኃጢአት በመራቅ፡፡**

ወደ እግዚአብሔር ከመቅረባቸው በፊት ለ2 ቀናት ቀድሳቸው፣ ልብሳቸውን ይጠቡ፣ እድፋቸውን ያስወገወዱ፤ ይህን ካደረጉ በኋላ በ3ኛው ቀን እግዚአብሔርን ሊገናኙ ይሰብሰቡ/ይቅረቡ አለ፡፡

ወደ እግዚአብሔር ከመቅረብ በፊት ኃጢአትን በመናዘዝና በንስሃ መቀደስ/መታጠብ ያስፈለገበት ምክንያት እርሱ ወሰን የሌለው ታላቅ፣ ክቡርና እንከን የሌለበት ቅዱስ፣ ኃጢአትን የሚጠላ ስለሆነ ነው፡፡

ውጫዊ ሰውነትና ልብስን በንጽህና መጠበቅ ለሰውነት ጤንነትና ጠረን መልካም ቢሆንም በእግዚአብሔር ፊት ተፈላጊ የሆነው ውስጣዊ የልብ/የህሊና ንጽህናን ነው፡፡ የተለያየ ኃጢአት ሰርቶ/ሰውንና እግዚአብሔርን በድሎ ያንን ሳያስተካክሉ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ የልባችን ትኩረት ወደ ሌላ የሚያመራ፣ ህሊናችንም እየተካሰሰ የእግዚአብሔርን ቃል እንደሚገባ ማድመጥን የሚያውክ ይሆናል፡፡

እርሱ ፍጹም ቅዱስ ስለሆነ ኃጢአትን እንደሚጠየፍ አውቀን ወደ እርሱ ስንቀርብ ራሳችንን መርምረን የኃጢአትን ቆሻሻ በንስሃ በማሰወገድ መሆን የኖርበታል፤ ንስሃ መግባት እግዚአብሔርን ማክበር እንደሆነ በተጨማሪ የሚያረጋግጥልን ኢያሱ 7፡19፣ ላይ "ኢያሱም አካንን ልጄ ሆይ ለእስራኤል አምላክ ለእግዚአብሔር ክብር ስጥ ለእርሱም ተናዘዝ፣ ያደረግኸውን ሳትደብቅ ንገረኝ" ማለቱ ነው፡፡ (ሉቃ15፡7)

ወደ እግዚአብሔር ለማንኛውም ጉዳይ ሲቀርቡ በተገቢ አክብሮታዊ አቀራረብ (በመንበርከክ፤ ወደ መሬት ዝቅ ብሎ በመስገድ፤ እጆችን ወደ ላይ በማንሳት፤ እና በተገቢ የአክብሮት አነጋገር በመጠቀም) መሆን አለበት፡፡ ዘፍ 18፡1-4፤27

ወደ እግዚአብሔር ሲቀርቡ ቢቻል በጸጥታ ስፍራ፤ ራስን አረጋግቶ (ሌላ ጉዳይ/ በልብ ያለ የሚያስቸኩል ጉዳይ በማስወገድ) መሆን አለበት፡፡

የእግዚአብሔር ቃል በውስጣችን ፍሬ እንዳያፈራ የሚያደርግ ጭንጫ/እሾካማ መሬት ዓይነት እልከኝነት/የልብ ድንዳኔ፣ ዓለማዊ ምኞት፤ ማጉረምረምና ላለማመን ተዘጋጅቶ መምጣትን በማስወገድና ልባችንን አለስልሰን በማዘጋጀት መሆን ይኖርበታል፡፡ ሉቃ 8፡ 18፤ ኢሳ 66፡2፤

ሀ. ቃሉን ስናጠና እንደ ህይወታችን ጌታ ቃል፣ በአክብሮትና በፍርሀት ትኩረት ሰጥቶ በጥሞና በመጠማት ማጥናት ነው፡፡ ሰውን እንደመሳሪያ ተጠቅሞ ሲናገረን ያኔም በተመሳሳይ ሁኔታ ማክበር ነው፡፡ እግዚአብሔር ብዙ ህዝብ በተሰባሰበበት ጉባኤ ሲናገርም ለተወሰኑ ሰዎች ሳይሆን ለብዙ ሰዎች ነው ሚናገረው፡፡ መንፈስ ቅዱስ እንደ ወንዝ ውሃ ነው የቃሉን በረከት የሚያፈሰው፡፡ የወንዝ ውሃ ደግሞ ቆሞ አይጠብቅም፡፡ አልፎ ይሄዳል፡ ፡ አእምሯችን ሳይከፋፈል በንቃት ስናደምጥ ለግላችን የሚናገረው የበረከት ቃል አያመልጠንም፡፡

እግዚአብሔር ህዝቡ በተሰባሰበበት ጉባኤ ሲገኝ ሁሉም የባርኮቱ ሙላት እንደያዘ ነው የሚገኘው፡፡ (የፈውስ፤ የነጻ መውጣት፤ የእድገት፤ የመንፈሳዊ ምድራዊና አካላዊ አእምሯዊ … በረከቶች)፡፡ ሁሉን ተራ በተራ ይለግሳል፡፡ ምንም ሳንቀበል ወይም ጥቂት ተቀብለን እንዳንወጣ በእምነትና በንቃት መጠባበቅና መከታተል አለብን፡፡

ለ. እግዚአብሔር በቃሉ እንደተናገረው/እንደሚፈልገው ለመለወጥ/ለመተግበር/ለመኖር ልብን አዘጋጅቶ መቅረብ፡፡

ሐ. የእግዚአብሔርን ቃል ለመማር ሲቀርቡ፣ ልክ እንደተማሪ ራሳችንን አዘጋጅተን መሆን አለበት፡፡ ተምሮ የጨረሰና ቃሉን ሁሉ በመፈጸም ፍጹም ቅዱስ የሆነ ሰው መምሰል የለብንም፡፡ የሚናገረንን አዲስ ነገር በማስታወሻ እየያዝን እቤት ወስደን ከሚመሳሰለው የቃሉ ክፍል ጋር አብረን በማኖር በሚያስፈልገን ጊዜ ለራሳችን እየተጠቀምንበት ሲያስፈልግ ለሌሎችም ማካፈል እንዲያስችል አመቻችቶ ማቆየት ይጠይቃል፡፡

**2) እግዚአብሔርን ማክበር እርሱን በመፍራት ይገለጣል፤ ዘዳ 5፡23-25-28-29** ኢሳ 8፡12-13፣

እግዚአብሔር ግርማ ሞገሱ ታላቅ ነው፤ የስልጣኑ፣ የኃይሉ ታላቅነት ወሰን የለውም፡፡ እርሱ የዘጋውን የሚከፍት የከፈተውም የሚዘጋ የለም፡፡ የወደደውን ቢያደርግ የሚከለክለው የለም፡፡ ሰማይና ምድርን በውስጣቸው ያለውን ሁሉ የፈጠረ ነው፡፡ ወደ ከፍታም ሊያወጣ፣ ዝቅም ሊያደርግ ይችላል፡፡ ስለዚህ ሊፈራ ይገባዋል፡፡

ዘፀ 5፡13–15–16–18፣ እስራኤላዊያን በግብጽ ምድር ግፍ በበዛባቸው ጊዜ መፍትሂ ባያገኙም ፈርዖን ፊት በአክብሮትና በፍርሃት ቀርበው አቤቱታቸውን አሰምተዋል፡፡

ዘፀ 5፡19–21፣ ነገር ግን እነዚሁ ሰዎች ወደ ሙሴና አሮን ፊት ሲቀርቡ አክብሮትና ፍርሃት በማሳየት ፈንታ ተራገሙ፣ ተቆጡም፤ በድንጋይ ሊወግሩ ፈለጉ፡፡ ሙሴና አሮን እኮ እግዚአብሔር ራሱ የላካቸው ተወካዮቹ ናቸው፡፡ እግዚአብሔር እኮ ሙሴን ለፈርዖን እንደ አምላኩ አድርጎታል፤ ወደ እግዚአብሔር ሰራተኞች ሲቀርቡ እኮ ወደ እግዚአብሔር መቅረባቸው ነው፡፡ለምንድነው ሙሴንና አሮንን ያላከበሩት፤ መከባበር ከአገልጋዮችም ከተገልጋዮችም ይጠበቃል፡፡

ርስታቸውን ለመውረስ ወደ ከነዓን ምድር ይጓዙ የነበሩት እስራኤላዊያን የተለያየ ያልጠበቁት ፈተና በገጠማቸው ጊዜ ወደ እግዚአብሔርና ሰራተኞቹ ፊት ይቀርቡ የነበረው በማጉረምረም፣ በማማረር፣ በቁጣ፤ ሊጣሉ ድንጋይ በማንሳት ነበር፡፡ እንደዚህ እግዚአብሔር ፊት ይቀርቡ የነበሩ ሰዎች ሄዱ ሄዱና በምድረ-በዳ ሞተው ሲያልቁ፣ ጥቂቶች ብቻ ወደ ተሰጣቸው ተስፋ ምድር ገቡና ወረሱ፡፡ (ዘፀ14፡10-12 ፣15፡ 24፣ 17፤1-3፣) (ሚልክ 4፡2-3፣ ማቴ10፡28፣ ዘፍ 39፡9)፣

እግዚአብሔር ለሕዝቡ አባት፣ ወዳጅ፣ አዳኝ፣ ረዳትም ጋሻም….ቢሆንም እርሱ አምላክ ነው፡፡ ለክብሩ የሚቀና/ የሚባላ እሳት ስለሆነ መፈራት ይገባዋል፡፡ ቃሉም ህያውና የሚሰራ ስለሆነ ክብር የሚገባው ነው፡፡ ሰው የእግዚአብሔርን ቃል ከናቀ ሌላ ተስፋ የለውም፡፡

ዳን 3፡13-18፣ 28፤ ሲድራቅ ሚሳቅና አብደናጎ የሚያስፈሩትን ንጉስና ሰራዊቱ መኳንንቱ ይልቅ ከእግዚአብሔር በቀር ለሌላ ለማንንም አንሰግድም በማለት ለእርሱ ብቻ የተገባውን አምልኮ ለማንም አንሰጥም ብለው እርሱን በመፍራት ለእርሱም በመስገድ ስለጸኑ በከለዳዊያን ምድር አከበሩት፡፡ ሰው የሚፈራቸው ፍጥረታትና ክስተቶች ሁሉ እርሱ የፈጠራቸውና የሚቆጣጠራቸው ናቸው፡፡

**3/ ዘሁ 14፡6–10፣ እግዚአብሔርን ማክበር የእግዚአብሔርን ቃልና ማንነት ሁሉ ወደር አልባ ታላቅነት በማመን ይገለጣል፤**

የተሰፋይቱን ምድር/ እግዚአብሔር ማርና ወተት የምታፈስ ናት ያላት ምድር ለመውረስ በጉዞ ላይ የነበሩት እስራኤላዊያን ወደ ሚወርሱት ምድር ሲቃረቡ ምድሪቱን የሚሰልሉ ሰዎች ልከው ከሰላዮቹ ሪፖርት ከሰሙ በኋላ ለሁለት ተከፈሉ፤

የ1ኛው ወገን (ከህዝቡ 99.9% በላይ የሚሆኑት)፣ ቃል እንዲህ ማጠቃለል የቻላል፡፡ የምንሄድባት ምድር ህዝብ ቁጥራቸው ብዙ ነው፤ ግዙፎችና ኃያላን ናቸው፤ እኛ በፊታቸው እንደ አንበጣ ነበርን፡፡ ከተሞቻቸው የተመሸጉና ትላልቆች ናቸው፡፡ የብረት ሰረገሎች አሉዋቸው፤ ስለዚህ ልናሸንፋቸው አንችልም፡፡ ይልቁንም እኛ እናልቃለን፤ ልጆቻችንና ሚስቶቻችን ይማረካሉ በማለት ደመደሙ፡፡

የ2ኛው ወገን (ሁለት ሰዎች ብቻ የያዘ ወገን) ቃል፡-
በምድሪቱ ያሉት ሰዎች በ1ኛው ወገን እንደተነገረው ጥንካሬ አላቸው፤ ግን የምድሪቱን ሰዎች ጥላቸው ተገፏልና አትፍሯቸው፣ እግዚአብሔር ከኛ ጋር ስለሆነ እናሸነፋለንና እንውጣ የሚል ነበር

እግዚአብሔርም የሁለቱም ወገን ድምዳሜ ከሰማ በኋላ እንዲህ አለ፡፡
ዘሁ14፡11፣ 20-23፣ ""ምድርን ሁሉ የሞላው ክብሬን አይተው፤ በግብጽና በምድረ-በዳ በፊታቸው/ዓይናቸው እያየ ደረግሁትን ድንቅ ታዓምራት ሁሉ አይተው እስከመቼ

ይንቁኛል፤" የማያምኑብኝስ እከመቼ ነው?" ……ያለማመናቸው ኃጢአት ጽዋ በፊቱ ሞላ፤ ስለዚህ **"የናቀኝ ማንኛውም ሰው ምድሪቱን አያያትም አለ፣"**

እግዚአብሄርን አለማመን ማለት፡-

-እግዚአብሔርን መናቅ ነው፤ ኃይሉን/ችሎታውን አሳንሶ ማየት፡

-እግዚአብሔር ተናገረው ነገር ውሸቱን ነው/ያለው አይሆንም ማለት ነው፤ ዮሐ5፡10

-እግዚአብሔር ከገጠመን ችግር/ብርቱ ሰልፍ/ውስብስብ ሁኔታ ሊያድነን አይችልም፤ የእግዚአብሔር ችሎታ ያንሳል እንደማለት ነው፡፡

- ወይም እግዚአብሔር ይችላል ግን ሊያድነኝ አይፈልግም እንደማለት ነው፤

-አባታችን አብርሐም ምንም ተስፋ ሰጪ ሁኔታ በሌለበት በተስፋ **አምኖ እግዚአብሔርን በማክበር** የብዙዎች አባት ሆነ፤ ሮሜ 4፡18-20፤

-12 ዓመት ደም ሲፈሳት የነበረችው ሴት በግል ስለ እርሷ መፈወስ በመጽሀፍ ቅዱስ ተጽፎ አላነበበችም ወይም ትነቢት አልተነገራትም፤ የጌታን የማዳን ታላቅነት ሰምታ ከመረዳት ተነስታ እኔም ያድነኛል ብላ አምና ዳነች፡፡

- እምነት ማለት አግዘዚአብሔር በምንም ተስፋ አስቀራጭ ውስብስብ ሁኔታ ውስጥ ብሆንም ይደርስልኛል ብሎ እርግጠኛ መሆን ነው፡፡ ሮሜ 12፡18-21

- በመጽሀፍ ቅዱስ የተጻፈውን የተስፋ ቃል ሁሉ ለእኔም ነው ብሎ ማመን፤ በታማኝ ነቢያቱ የሚናገረውን የትንቢት ቃል ማመንን ያጠቃልላል፡፡ 2ዜና 20፡20 (2 ነገ 7:1-2)

**4/ እግዚአብሔርን ማክበር የእግዚአብሔርን ቃልና ፈቃዱን በመታዘዝ ይገለጣል፤**

1 ሳሙ15፡22-23፤ እግዚአብሔርን መታዘዝ ቃሉን በጥንቃቄ ከመስማት ይጀምራል፡፡ ከእርሱ እንደሰሙት ሳይጨምሩ፣ ሳይቀንሱ፣ ሳያሻሽሉ መተግበር ከሰው ይጠበቃል፡፡

ሰው ጌታው አድርግ ያለውን በመታዘዝ ሲያደርግ እግዚአብሔርን ያከብራል፤ እግዚአብሔርም ደስ ይሰኝበታል፤

መታዘዝ፡- ይሄ በሁለት ሊከፈል ይችላል፡፡ ኃጢአት ማድረግን ትቶ በቅድስና መኖርና የመንግስቱን ስራ በመስራት፡፡ እንደ ሰሙት ቃል መለወጥ እግዚአብሔር ከሰው ይጠብቃል፡፡

- በዕለት ተዕለት ኑሮ ከቃሉ እንደተማሩት መልካም ማድረግን በመለማመድ መኖር ነው፤ ሰዎች አሮጌው ልማድ/ክፉ ፍሬ አስወግደው የጌታ ኢየሱስ ተከታዮች መሆናቸውን የሚገልጥ መልካም ፍሬ በማፍራት በህይወታቸው መልካም የሆነ የባሕርይ ለውጥ ሲያዩ እግዚአብሔር ይከብራል፡፡ ማቴ 5፡16፣ ዮሐ 15፡8

- ዮሐ 17፡4፤ እግዚአብሔር የሰጠውን የአገልግሎት ኃላፊነት/ስራ በትጋትና በታማኝነት በመፈጸም መወጣት ነው፤ የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማር፣ በተሰጡት የጸጋ ስጦታ በትጋት መስራት፡፡ የእግዚአብሔርን መልካምነት አምኖ በጎነቱን መናገር፣ የምልጃ ጸሎት መጸለይ… ያካትታል፡፡

- ሰው እግዚአብሔር ድምጽ በማሰማት አድርግ ያለውን አጣርቶ ሰምቶ ሳያዛባ በማድረግ, 1ሳሙ 15፡3፣ 7-9፣ 22-23፣ ዘዳ 5፡27-28-29፣ 2ቆሮ 7፡1

- በማንኛውም ከባድ የውጊያ ሁኔታ ውስጥ ቢኮን ታግሶ እግዚአብሔርን **በማመስገን መጠበቅ** ነው፤ በምድራዊ ኑሮ የተለያየ ውጣ ውረድ ቢገጥምም ከእግዚአብሔር አብሮነት የሚስተካከል/የሚበልጥ ነገር ስለሌለ ዋናውን ላለማጣት በመጠንቀቅ፡፡ መዝ 50፡23፣ ፊሊጵ 4፡6፣ 1ተሰ5፡18፤

- እግዚአብሔር የሰጠው ሰውነት አካል ክፍሎችን ላልተቀደሰ ተግባር ላለማዋል በመጠንቀቅ፡- 1ቆሮ 6፡19-20

- የሚያደርጉትን ማንኛውም ነገር እግዚአብሔርን ሊያከብር በሚችል መንገድ በማድረግ ለሌሎች በአንዳች ረገድ መሰናክል እንዳይሆን በመጣር፡፡ 1ቆሮ 10፡31-32፣

- ከአፍ የሚወጣ ቃል፡- በምስጋናና ውዳሴ ዝማሬ ድንቅ ሥራውን በማነሳሳት ማድነቅ፣ ማወደስ፣ ማምለክ መዝ 66፡1-2፣

ወደ እግዚአብሔር በሚደረግ ጸሎት እርሱ የበጎ ስጦታና በረከት ሁሉ ምንጭ መሆኑን እውቅና በመስጠት፡፡

- በሰጠው ስጦታ/ችሎታ/ሀብት/ጉልበት ለእግዚአብሔር ቤት ሥራ የሚገባውን ልዩልዩ ስጦታ በመስጠት፤ ምሳ 3፡9-10፣
1ሳሙ2፡29-30 "...የሚያከብሩኝን አከብራለሁ፣ የሚንቁኝ ይናቃሉ" እግዚአብሔርን ማክበር ከማንኛውም የቅርብ ቤተሰብ/ወዳጅ እና ከራስ ህይወትና ንብረት ይልቅ እግዚአብሔርን በመውደድና በማክበር ይገለጣል፡፡ ሉቃ 14፡25-33፤ ማቴ 22፡36-37፣

©ኤልያስ ታሪኩ (ዶ/ር) 2018 ዓ.ም.